የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No. 15
ADDIS ABABA 5th February, 2008

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፬/፪ሺህ ዓ.ም

ለመስኖና ድሬይኔጅ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያአዋጅ … ገጽ ፬ሺ፲፬

CONTENTS

Proclamation No. 564/2008

International Development Association Financing Agreement for Irrigation and Drainage Project Ratification Proclamation Page 4014

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፬/፪ሺህ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመስኖ የድሬይኔጅ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚ ውል ፷፭ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር /ስድሣ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር/ ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፲፫ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፰ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «ለመስኖና ድሬይኔጅ ፕሮጀክት ማስፈ ፀሚያ የሚውል ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደ ቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፬/፪ሺህ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 564/2008.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan in an amount not exceeding SDR 65,600,000 (sixty five million six hundred thousand Special Drawing Rights) for financing irrigation and drainage project, was signed in Addis Ababa on the 13th day of July 2007;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 17th day of January, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Irrigation and Drainage Project Ratification Proclamation No.564/2008".

## የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ ጁላይ ፲፫ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 4333ET የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፷፭ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር /ስድሣ አምስት ሚሊዮን ስድ ስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Number 4333ET signed in Addis Ababa on the 13th day of July 2007 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of SDR 65,600,000 (sixty five million six hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 5th day of February, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**